እኔ ወደ ሰማይ ባረግኩበት ምሽት ኢብራሂምን አገኘኋቸው። እንዲህም አሉኝ ‹ሙሐመድ ሆይ! ለኡመትህ ከኔ የሆነን ሰላምታን አቅርብ! ጀነት ምርጥ አፈርና ጣፋጭ ውሃ እንዳላት

ከኢብኑ መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "እኔ ወደ ሰማይ ባረግኩበት ምሽት ኢብራሂምን
አገኘኋቸው። እንዲህም አሉኝ ‹ሙሐመድ ሆይ! ለኡመትህ ከኔ የሆነን ሰላምታን አቅርብ! ጀነት ምርጥ አፈርና ጣፋጭ ውሃ እንዳላት ጀነት ገላጣ (ዛፍ የሌለባት) ሜዳ እንደሆነችና የሚተከልባትም ሱብሓነላህ ወልሐምዱሊላህ ወላኢላሃ ኢለሏህ ወሏሁ አክበር [በማለት]
እንደሆነ ንገራቸው።›"»
[በማመሳከሪያዎቹ ሐሰን ነው።] [ቲርሚዚ ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በኢስራእና ሚዕራጅ ምሽት የአላህ ፍፁም ወዳጅ የሆኑትን ኢብራሂምን ዐለይሂ ሰላም እንዳገኙ ተናገሩ። ለርሳቸውም «ሙሐመድ ሆይ! ለኡመትክ የኔን ሰላምታ አድርስ! ጀነት አፈሯ ምርጥና ውሃዋም ጨውነት የሌለው ጣፋጭ ውሃ እንደሆነ፤ ጀነት ዛፍ የሌለበት ቀጥ ያለና ሰፊ ሜዳ ሲሆን የጀነት ተክልም ምርጥ ንግግሮችና ቀሪ የሆኑ መልካም ስራዎች እንደሆኑ እነርሱም: "ሱብሓነላህ" "ወልሐምዱሊላህ" "ወላኢላሃ ኢለሏህ" "ወሏሁ አክበር" እንደሆኑና አንድ ሙስሊም በደጋገማቸው ቁጥር ጀነት ውስጥ ተክል እንደሚተከልለት ንገራቸው።» አሉ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/3791